# የመጽሐፍ ቅዱስ አከፋፈል

## መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት በትውፊትም ሆነ በዘመናውያን ሊቃውንት የተለመደውን አከፋፈል መከተሉ ጠቃሚ ነው። ይህ አከፋፈል ከእያንዳንዱ የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍል ጋር ተገቢ የሆነ ት ውውቅ እንዲኖረን ከማደረጉም በላይ አንዱ መጽሀፍ ከሌላው መጽሀፍ ጋር ያለውን ግንኙነትም እንድናስተውል ያደርጋል።

ብዙ ጊዜ ከምእመናን የሚሰማው ችግር አንዱን የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍል ለማንበብ ስንሞክር እን ግዳ መሆኑ ነው። ይህ አይነቱ ችግር የሚመነጨው አጠቃላይ የመጽሀፍ ቅዱስን መልእክት ብሎ ም የዚያን የምናነበውን መጸሐፍ አጠቃላይ ሀሳብ ለመጨበጥ ካለመቻል ነው። ለዚህ ምሳሌ የም ናደርገው በከተማችን ውስጥ ያለን አንድ መንገድ ነው። ያንን መንገድ በሚገባ ልናውቀው የምን ችለው ከሌላው የከተማው ክፍል ጋር አነጻጽረን ነው። በዚሁ መልክ የመጽሀፍ ቅዱስን አከፋፈ ል በሚገባ ካስተዋልን መጻህፍቶቹ በየትኛው ክፍል በእነማን ጊዜ እንደነበሩ ለማወቅ እንችላለን።

## ሀ. የመጽሀፍ ቅዱስ አጠቃላይ አከፋፈል

መጽሀፍ ቅዱስ በውስጡ የያያዛቸው መጻህፍት በሁለት አበይት ክፍሎች ይከፈላሉ። እነርሱም የ ብሉይ ኪዳን መጻህፍትና የአዲስ ኪዳን መጻህፍት ናቸው።

### 1. የብሉይ ኪዳን መጻህፍት።

የብሉይ ኪዳን መጻህፍት ከክርስቶስ መምጣት በፊት በነበሩት አበው ነቢያትና ነገስታት የተጻፉ መጻህፍት ናቸው። ስለብሉይ ኪዳን ልናውቃቸው የሚገባን አራት ነጥቦች፤

1.1. ብሉይ ኪዳንን በእስራኤላውያን በኩል የሰጠው ራሱ እግዚአብሄር ነው።
1.2. ብሉይ ኪዳን የመሲሁን መምጣት በምሳሌ በትንቢትና በመስዋእት የገለጠ ነው።
1.3. ብሉይ ኪዳን አዲስ ኪዳንን በውስጡ የሸሸገ ነው።
1.4. ብሉይ ኪዳን በመሲሁ መምጣት ፍጻሜ አግኝቶአል እንጂ አልተሻረም።

### 2. የአዲስ ኪዳን መጻህፍት

የአዲስ ኪዳን መጻህፍት ከክርስቶስ በተማሩ ሀዋርያትና በእነርሱ ረዳቶች (አርድእት) የተጻፉ መ ጻህፍት ናቸው። የክርስቶስን ልደት ትምህርት መከራ ሞትና ትንሳኤ እንዲሁም የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የነበራቸውን ህይወት እነርሱንም ለማነጽ የተላኩትን መልእክታት የያዙ ናቸው። ስ ለአዲስ ኪዳን ልናውቃቸው የሚገቡን አራት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

2.1. አዲስ ኪዳን በክርስቶስ ደም መፍሰስ የተመሰረተውን አዲስ ኪዳን የሚገልጥ ነው
2.2. አዲስ ኪዳን ዋናው መልእክቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
2.3. አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ትርጉዋሜና ፍጻሜ ነው።
2.4. አዲስ ኪዳን በመምጣቱ ምክንያት ፊተኛውን አስረጅቶታል።

## 1.1. <u>የብሉይ ኪዳን መጻህፍት አከፋፈል</u>

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። አከፋፈላቸው በዘመንና በጽሑፉ ቸው ይዘት ነው። ይህ አከፋፈል ከአይሁድ አከፋፈል ለየት ይላል። አይሁድ ብሉይ ኪዳንን በ ሦስት ክፍሎች ይከፍሉዋቸዋል። እርሱም ህግ (ቶራህ) ጽሁፋት (ክቱቢም) ነቢያት ናቸው። ወንጌ ላውያኑ ይህን የአይሁድን አከፋፈል ብዙ ጊዜ በትምህርታቸው ጠቅሰውታል። ለምሳሌ ቅዱስ ሉ ቃስ «ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻህፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጎመላቸው» ብ ሎአል። ሉቃ 24፥26።

ይህ አሁን የምናየው አከፋፈል የብሉይ ኪዳንን መጻህፍት በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይመድባቸ ዋል። እነዚህም፥

1.1.1. የኦሪት (የህግ) መጻህፍት
1.1.2. የታሪክ መጻህፍት
1.1.3. የጥበብ (የቅኔና የመዝሙር) መጻህፍት
1.1.4. የትንቢት መጻህፍት ናቸው።

1.1.1. **የኦሪት (የህግ) መጻህፍት።** የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻህፍት የኦሪት መጻህፍት ወይም በ ቤተ ክርስቲያናችን ቋንቋ አምስቱ ብሄረ ኦሪት ይባላሉ። እነዚህም ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም ያሉት ናቸው። እነዚህን መጽሀፍ ቅዱስ ራሱ የሙሴ መጻህፍት የህግ መጻህፍት እያለ ይጠራቸዋል። ይህም ከእብራይስጡ የተወሰደ ነው። አይሁድ በጥቅሉ «ሴፈር ሃቶራ» ወይም «ሃ ቶራ» የህግ መጽሀፍ ብለው ነው የሚጠሩአቸው። በግሪኩ «ፔንታቱኮስ» በሚል ስያሜ ይታወቃ ሉ። አምስት ቅጾች እንደማለት ነው። መጻህፍቱ ከአለም መፈጠር ጀምሮ እስከ ሙሴ እረፍት ድረስ ያለውን የአበውን ታሪክና የእስራኤልን ከባርነት ነጻ መውጣት ይናገራሉ።

1.1.2. **የታሪክ መጻህፍት።** ከመጽሀፈ ኢያሱ ጀምሮ እስከ መጽሀፈ አስቴር ድረስ ያሉትን መጻህ ፍት በሙሉ ያጠቃልላል። እነዚህ መጻህፍት ምድረ ርስትን ከመውረስ ጀምሮ እስከ ባቢሎን ምር ኮ ድረስ ያለውን የእስራኤላውንያንን ታሪክ የሚናገሩ ናቸው።

1.1.3. **የጥበብና የቅኔ የመዝሙር መጻህፍት።** እነዚህ ጽሁፋት በማለት በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የ ሚጠሩት ከመጽሀፈ ኢዮብ እስከ መሀልየ መሀልይ ያለውን ያጠቃልላል። እነዚህ በመዝሙር በ ቅኔና በጥበባዊ አነጋገር የተገለጡ ውዳሴዎች ምክሮች እና ቅኔዎች ናቸው። ከመጽሐፈ ኢዮብና ከመዝሙረ ዳዊት በስተቀር ሌሎቹ በንጉሱ በሰሎሞን የተጻፉ ናቸው።

1.1.4. **የትንቢት መጻህፍት።** ከእስራኤል መከፈል በኋላ በባቢሎን ምርኮ ዋዜማና በምርኮው ወቅ ት በነበሩ ነቢያት የተነገሩ ትንቢቶች ናቸው። መጽሀፍ ቅዱስ እነዚህን ጽሑፎች ነቢያት እያለ ይጠራቸዋል። እነዚህ የትንቢት መጻሕፍት እንደገና ለሁለት ይከፈላሉ።

1.1.4.1 **ዐበይት ነቢያት።** ዐበይት ነቢያት የሚባሉት አራቱ የመጀመሪያዎቹ የትንቢት መጻ ሕፍት ኢሳይያስ ኤርምያስ ህዝቅኤልና ዳንኤል ናቸው። ዐበይት መባላቸውም ከሚያነሱት ርእሰ ጉዳይ ስፋት ነው እንጂ ከነቢዩ ማነስና መተለቅ አንጻር አይደለም።

1.1.4.2 **ደቂቀ ነቢያት።** ከአበይት ነቢያት ውጭ ያሉት አስራ ሁለት መጻሕፍት ደቂቀ ነቢ ያት ይባላሉ። እነዚህም ትንቢተ ሆሴእ እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ያሉት ናቸው።

ማሳሰቢያ። የብሉይ ኪዳን አከፋፈል በአብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ስምምነት ቢኖርም ቁጥራ ቸው ላይ ግን ሰፊ ልዩነት አለ። ፕሮቴስታንቶች የአይሁድን አቆጣጠር ሲቀበሉ በግሪክ ኦርቶዶክ ስ፣ በካቶሊክና በኦሬንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ከፍተኛ የሆነ የአቆጣጠር ልዩነ ት አለ። በኦሬንታሎችም ዘንድ ቢሆን አንድ አይነት ስምምነት የለም። ይህን የቁጥር ልዩነት በ ተመለከተ በሌላ ክፍለ ጊዜ በሰፊው እናየዋለን።

1.2. <u>የአዲስ ኪዳን መጻህፍት አከፋፈል።</u>

ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን መጻህፍት የአዲስ ኪዳን መጻህፍትም በአራት ክፍሎች ይከፈላሉ። አከ ፋፈላቸውም ከጽሁፋቸው ይዘትና የአጻጻፍ ስልት ጋር የተያያዘ ነው።

1.2.1. የወንጌል ክፍል። የመጀመሪያዎቹ አራት የአዲስ ኪዳን መጻህፍት ወንጌላት ይባላሉ። ወን ጌል (ኢባንጌሊዮን) ማለት መልካም ዜና ማለት ነው። እነዚህ መጻህፍት በተለያየ መልኩ አንዱ ን የክርስቶስን ታሪክ በተለያየ አቅጣጫ የሚናገሩ ናቸው። በውስጣቸውም የክርስቶስን ልደቱን ጥ ምቀቱን ትምህርቱን ህማሙን ሞቱንና ትንሳኤውን ይተርካሉ።

1.2.2. የታሪክ ክፍል። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተተው የወንጌሉ ቀጣይ አድርጎ ሉቃስ የጻፈው የ ሐዋርያት ስራ ነው። ይህ መጽሐፍ የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ተከትሎ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳ ሌም በይሁዳ እስከ ዓለም ዳርቻ እንዴት እንደተስፋፋች የሚተርክልን ነው።

1.2.3. የመልእክት ክፍል። በዚህ ውስጥ የሚካተቱት ጳውሎስና ሌሎችም ሐዋርያት በየሥፍራው የላኩዋቸው መልእክታት ናቸው። በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት ጳውሎስ አስራ አራት መልእክታ ትን የጻፈ ሲሆን ሌሎቹን ሰባት መልእክታት ደግሞ ጴጥሮስ ዮሀንስ ያዕቆብና ያስቆሮቱ ያይደለው ይሁዳ ጽፈውታል። እነዚህ ሰባት መልእክታት አጠቃላይ መልእክታት (ካቶሊክ) መልእክታት ተ ብለው ይታወቃሉ። እንዲህ መባላቸውም በአጠቃላይ ለክርስቲያኖች የተጻፉ እንጂ ለአንድ ውሱ ን ህዝብ ወይም ቦታ ወይም ግለሰብ የተጻፉ ባለመሆናቸው ነው።

ጳውሎስ የጻፋቸው መልእክታት ለአብያተ ክርስቲያናት የላካቸው መልእክታትና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የላካቸው መልእክታት በመባል ይከፈላሉ። በግለሰብ ደረጃ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የ ላካቸው መልእክታት ሁለቱ ለጢሞቴዎስ የተላኩ ሲሆኑ ቀሪዎቹ ለቲቶና ለፊልሞና የተላኩ ናቸ ው። በሌላ በኩል ደግሞ የጳውሎስን መልእክታት ከእስር ቤት የተላኩ መልእክታትና በአገልግሎ ት ሳለ የተላኩ መልእክታት ብለው የሚከፍሉአቸውም አሉ።

1.2.4. የትንቢት ክፍል። በዚህ ክፍል ውስጥ የሚመደበው የዮሐንስ የመጨረሻው መጽሐፉ የሆነ ው ራእየ ዮሐንስ ነው። በደሴተ ፍጥሞ ስለወንጌል ታስሮ ሳለ ያየውን ነበር ዮሀንስ በመጽሐፍ የ ጻፈው።

# 1. ኦሪት ዘፍጥረት

## 1.1. ስያሜው፤

ስያሜውን የተወሰደው ከሰባ ሊ.ቃናት የግሪክ ትርጉም ነው።(200 ዓ.ዓ ገደማ) አይሁድ ግን በመጽ ሀፉ የመጀመሪያ ቃል «በመጀመሪያ» የሚለውን በመያዝ «በረሽት» ይሉታል።

## 1.2. ጸሐፊው፤

የጥንት ቤተ ክርስቲያን እንደመሰከረችው የዘፍጥረት ጸሐፊ ሙሴ ነው። ሆኖም ግን የተወሰኑ ም ንባባት በስተኋላ የተጨመሩ ይመስላሉ። ለምሳሌ 12፥6 ላይ « አብራምም እስከ ሴኬም ስፍራ እስከ ሞሬ የአድባር ዛፍ ድረስ በምድር አለፈ፤ የከነአን ሰዎችም በዚያን ጊዜ በምድሩ ነበሩ።» በማለት ይናገራል። ይህም በከነዐን የነበሩት ሰዎች ከምድሪቱ ከተባረሩ በኋላ የተጻፈ ይመስላል። ይህ ደግሞ የሆነው ከሙሴ እረፍት በኋላ ነው።

## 1.3. ቁልፍ ሰዎች፤

አዳምና ሄዋን አቤልና ቃየን ሴት ኖህ አብርሃምና ሳራ ይስሐቅና ርብቃ ኤሳው ያዕቆብ ራሔል ይሁዳና ወንድሞቹ ዮሴፍ።

## 1.4. ቁልፍ ቦታዎች

### 1.4.1. የአራራት ተራራ፤

ቦታው የዛሬዋ አርሜኒያ ካለችበት አካባቢ ነው። ቃሉ በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ አራት ጊ ዜ ተጠቅሶአል።እግዚአብሄር አለምን በጥፋት ውሃ በደመሰሰ ጊዜ ኖህ ቤተሰቦቹንና እንስ ሳትን ይዞ ወደ አዘጋጀው መርከብ ገባ፤ ውሃው ሲቆም መርከቢቱ በአራራት ተራራ ላይ አ ረፈች።

### 1.4.2. ባቤል፤

በጥንታዊት ባቢሎን (ሱሜር) ምድር ናምሩድ ከመሠረታቸው ከተሞች ዋናዋ ናት። ባቢሎና ውያን ባቤል በዋና አምላካቸው በማርዱክ እንደተመሠረተች ይናገራሉ። ሳርጎን በ2350 ኣ.ኣ ከተማዋን የደመሰሰ ሲሆን አዲሱን ዋና ከተማውን አካድን በመሰረተ ጊዜ አፈሩን ከባ ቢሎን እንደወሰደ ይነገራል። የከተማዋ ምስረታና ታዋቂው ግንብ በዘፍ 11፥1-11 በዝርዝር ተጠቅሶአል። ባቤል የሚለው ቃል « ባላል » ከሚለው የእብራይስጥ ቃል ተመሳሳይ መ ሠረት አለው። ትርጉሙም ድብልቅልቅ ግርግር ማለት ነው። ይህም የሰውን ትእቢት ለመ ቅጣት እግዚአብሔር ያመጣውን የቋንቋ መደባለቅ የሚያሳይ ነው።

### 1.4.3. የከለዳውያን ዑር፤

ታራና ልጁ አብርሃም የወንድሙ ልጅ ሎጥ የተወለዱበት ቦታ ነው። ቅዱስ እስጢፋኖስ ኡር በሜሶፖታሚያ (በሁለት ወንዞች መካከል) የዛሬዋ ኢራቅ ውስጥ እንደሆነ እንዲህ በ ማለት ጠቅሶአል። «የክብር አምላክ ለአባታችን ለአብርሃም በካራን ሳይቀመጥ ገና በሁለ ት ወንዞች መካከል ሳለ ታየና ከአገርህና ከዘመዶችህም ወጥተህ ወደማሳይህ ወደማንኛው ም ምድር ና አለው» ሐዋ 7፥2-4።

1.4.4. **ካራን፤**

**በዛሬዋ ቱርክ ከምትገኘው ከኤዴሳ ደቡብ ምስራቅ** 32 **ኪ.ሜ ላይ የምትገኝ ናት። አብርሃ ም ወደ ከነዐን ከመሄዱ በፊት የኖረው በዚህ ነው።ዘፍ** 11፥31**። የይስሐቅ ሚስት ርብቃ ከቤተ ሰቦቹዋ ጋር የኖረችውና ያዕቆብም ከኤሳው ኮብልሎ የሄደው** (29፥4) **ልያንና እህ ቱዋን ራሔልን ያገባው እንዲሁም ከብንያም በስተቀር ልጆቹ በሙሉ የተወለዱለት በዚህ ነው።** (29፥32-30፥24)

1.4.5. **ቤርሳቤህ፤**

**ከኢየሩሳሌም ደቡብ ምእራብ** 77 **ኪ.ሜ ላይ ርቃ የምትገኝ የውሃ ጉድጓድ በአጠገቡዋ ያ ለች ከተማና አቅራቢያዎቹዋ በዚህ ስም ተጠርተዋል።** (**ዘፍ** 21፥14) **የስሙ ትርጉም የሰባ ት በጎች ጉድጓድ ወይም የመሐላ ጉድጓድ እንደማለት ነው። ሦስቱም አርእስተ አበው አ ብርሃም** (**ዘፍ** 22፥19) **ይስሐቅ** (28፥10 **ያዕቆብ** (46፥1) **በዚህች ከተማ ተቀምጠዋል።**

1.4.6. **ቤቴል፤**

**ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን** 19 **ኪ.ሜ ላይ የምትገኝና ዛሬ ቴል ቤይቲን ተብላ የምትጠራ ከ ተማ ናት። አብርሃም በከተማዋ በስተምስራቅ በኩል ሰፈረ። ለእግዚአብሔርም መሠዊያ ሠራ።**(**ዘፍ**12፥8) **ከግብፅ ሲመለስ ወደዚህችው ከተማ ተመለሰ።**(13፥3) **ለያዕቆብ ቤቴል እ ግዚአብሔርን የተገናኘባት እግዚአብሔርንም ኤል ቤቴል «የቤቴል አምላክ» ብሎ የጠራበ ት ቦታ ነው።** (31፥13፤ 35፥7) **ከእናቱ ወገኖች ዘንድ ከካራን በተመለሰ ጊዜ ወደ ቤቴል መጥቶ መሰዊያን ሰራ፤ የቦታውንም ስም ቤቴል ወይም ቤት ኤል « የእግዚአብሔር ቤት ብሎ ጠራ።**( 35፥1-15)

1.4.7. **ግብፅ፤**

**የአባይን ወንዝ ተከትሎ ባለው ለም መሬት የነበረውን የአፍካ ምድር ያጠቃልላል። አርእ ስተ አበው አብርሃም** (**ዘፍ** 12፥20) **ያዕቆብ ከነአን በረሃብ ውስጥ ሲሆን ወደ ግብጽ ወርደ ዋል።** (42፥1) **ዮሴፍ ወንድሞቹ በምቀኝነት የሸጡት ወደዚሁ ምድር ነው።**(37፥25-36) **በመ ጨረሻም እስራኤል በሙሉ ወደዚህ ምድር መጥተው እስከሙሴ መነሳት ድረስ ኖረዋል።**( 46፥1-50፥26)

## በኦሪት ዘፍጥረት የዘመን ክልል ውስጥ የተከናወኑ ዐበይት ድርጊቶች

| ዘመኑ | የተከናወኑ ድርጊቶች | ታሪኩ በመ ጽሐፍ ቅዱ ስ ውስጥ |
|---|---|---|
| | ፍጥረት | 1፥1 |
| | የኖህ መርከብ መስራት | 6፥13 |
| 2500 | ግብፃውያን የፓፒረስ ወረቀትና ጽሁፍን በመፍጠር የመጀመሪያውን ቤተ መጻህፍት ፈጠሩ። በመካከለኛው ምስራቅ ያሉ ብረትን በመጠቀም የተለያዩ መሳሪያዎችን መስራት ጀመሩ። | |
| 2331 | ሳርጎን ሱሜሪያውያንን ድል በማድረግ የመጀመሪያው የአለም ገዢ ሆነ | |
| 2300 | ግብፆች ለመጀመሪያ ጊዜ ፈረሶችን ማስለመድ ጀመሩ፤ ዶሮ በባቢሎን ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ የቤት እንስሳት ሆኑ። ቀስት ለመጀመሪያ ጊዜ በጦርነት ላይ ዋለ። | |
| 2160 | አብርሃም ተወለደ | 11፥27 |
| 2100 | መስታወት ስራ በመሴፔጦሚያ ህዝቦች ተጀመረ፤ የመጀመሪያዎቹ ዚጉራት (እንደ ባቤል (ሰናኦር) ግንብ ያለ) መሰራት ተጀመረ፤ የመጀመሪያው መድሀኒት የሆነው ኤቲል አልኮሆል ለህመም ማስታገሻነት መጠቀም ተጀመረ፤ | |
| 2096 | አብርሃም ከነዐን ገባ | 12፥5 |
| 2066 | ይስሐቅ ተወለደ | 21፥1-7 |
| 2006 | ያእቆብና ኤሳው ተወለዱ | 25፥21-26 |
| 2000 | የአሜሪካ የጥንት ነዋሪዎች ከሰሜን እስያ ወደ ሰሜን አሜሪካ ፈለሱ፤ ከብቶችን ማርባትና የመስኖ ስራ በቻይና ተጀመረ፤በህንድ አገር ወናፍ ከፍተኛ ሙቀት ለመፍጠር በጥቅም ላይ ዋለ። | |
| 1929 | ያእቆብ ወደ ካራን ምድር ተሰደደ | 28፥5 |
| 1915 | ዮሴፍ ተወለደ | 30፥23 |
| 1898 | ዮሴፍ በባርነት ተሸጠ | 37፥36 |
| 1885 | ዮሴፍ በግብጽ ምድር ገዢ ሆነ | 41፥41 |
| 1805 | ዮሴፍ በግብጽ ምድር ሞተ። | 50፥26 |

## 1.5. የክርስቶስ ምሳሌና ጥላ የሆኑ፤

በገነት የተሰዋው በግ ዘፍ 3፥21።ኤፌ 1፥6
አዳም ሮሜ 5፥14
አቤል ዕብ12፥24
መልከ ጼዴቅ ዕብ 5፥5-10
ይስሐቅ ዕብ11፥16
የይስሐቅ በግ ዘፍ 22፥13።ሮሜ 3፥24
ዮሴፍ። 16፥14፤

## 1.6. አበው ለእመቤታችን የተረጎሙት።

ሳይዘሩባት ያበቀለችው ምድር ዘፍ1፥11
ሔዋን።2፥23፤3፥1-15
የኖህ መርከብ 6፥13
የአብርሃም ድንኳን 12፥8
እፀ ሳቤቅ 22፥13
የያዕቆብ መሰላል 28፥10-17

## 1.7. የመጽሐፉ አከፋፈል።

ኦሪት ዘፍጥረት በሁለት አቢይ ክፍል ይከፈላል። የመጀመሪያው ክፍል በምድር ላይ ከሰው መፈጠር ጀምሮ የተከናወነውን ይናገራል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ እግዚአብሄር አብርሃምን የእርሱ ዘሮች ለተለየ ሁኔታ መጠራታቸውን ይናገራል።

ሀ. ፍጥረትና ውድቀት እስከ ጥፋት ውሃ ውጤት (ዘፍ 1-11።)
1. የአለምና የሰው ዘር አፈጣጠር።(1-2)
2. የሰው ልጅ ውድቀት (3-5)
3. የጥፋት ውሀ (6-9)
4. የሰው ልጅ መበታተን (10-11)

ለ. የአብርሃም ዘር፤ ከቤተ ሰብ ወደ ነገድ።
1. አብርሃም (የአህዛብ አባት) 12-23
2. ይስሐቅ (የቃል ኪዳን ልጅ) 24-26
3. ያዕቆብ (የተግሳጽ ልጅ) 27-36
4. ዮሴፍ  (በመከራ የከበረ) 37-50

## ዝርዝር አከፋፈል

| | | |
|---|---|---|
| 1፥1–2፥3 | **እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ** | |
| | 1፥1-2 | **የፍጥረት መጀመሪያ** |
| | 1፥3-23 | **የፍጥረት ክንውን** |
| | 1፥24-31 | **የእንስሳትና የሰው አፈጣጠር** |
| | 2፥1-3 | **የተቀደሰው ሰባተኛ ቀን** |
| 2፥4-4፥26 | **የሰማይና የምድር ሁኔታ** | |
| | 2፥4-3፥24 | **የኤደን ገነት** |
| | 4፥1-26 | **የመጀመሪያው ቤተ ሰብ** |
| 5፥1-6፥8 | **የአዳም ትውልድ ታሪክ** | |
| | 5፥1-32 | **የአዳም ሐረገ ትውልድ** |
| | 6፥1-8 | **የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ልጆች** |
| 6፥9-9፥29 | **የኖህ ታሪክ** | |
| | 6፥9-8፥22 | **የጥፋት ውሃ ታሪክ** |
| | 9፥1-17 | **የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ከኖህ ጋር** |
| | 9፥18-29 | **የካም ኃጢአት** |
| 10፥1- 11፥9 | **የሴም የካምና የያፌት ታሪክ** | |
| | 10፥1-32 | **የነገዶች ዝርዝር** |
| | 11፥1-9 | **የባቤል ግንብ** |
| 11፥10-26 | **የሴም ታሪክ** | |
| 11፥27- 25፥11 | **የታራ ትውልድና የአብርሃም ታሪክ** | |
| | 11፥27-12፥9 | **የአብርሃም መጠራት** |
| | 12፥10-20 | **አብርሃም በግብጽ** |
| | 13፥1-18 | **የአብርሃምና የሎጥ መለያየት** |
| | 14፥1-24 | **የአብርሃም ሎጥን መታደግ** |
| | 15፥1-21 | **የቃል ኪዳን ተስፋ** |
| | 16፥1-16 | **የእስማኤል ልደት** |
| | 17፥1-27 | **የግዝረት ቃል ኪዳን** |
| | 18፥1-19፥38 | **የሰዶም መደምሰስ** |
| | 20፥1-18 | **ሣራና አቤሜሌክ** |
| | 21፥1-21 | **የይስሐቅና የእስማኤል መለያየት** |
| | 21፥22-34 | **ከአቤሜሌክ ጋር ስምምነት** |
| | 22፥1-24 | **የይስሐቅ ለመሥዋዕት መቅረብ** |
| | 23፥1-20 | **የሣራ ሞትና መቀበር** |
| | 24፥1-67 | **የርብቃ ለጋብቻ መታጨት** |
| | 25፥1-11 | **የአብርሃም የመጨረሻዎቹ ቀናት** |

25፥12-18 የእስማኤል ታሪክ

25፥19-35፥29 የይስሐቅ ትውልድና የይስሐቅና የኤሳው ታሪክ

| | |
|---|---|
| 25፥19-35 | የኤሳውና የያዕቆብ አነሣሥ |
| 26፥1-33 | ይስሐቅና ፍልስጤማውያን |
| 26፥34-28፥9 | የያዕቆብ ኤሳውን ማታለል |
| 28፥10-22 | የያዕቆብ እግዚአብሔርን በቤቴል ማግኘት |
| 29፥1-30 | የያዕቆብ ራሔልንና ልያን ማግባት |
| 29፥31-30፥24 | የያዕቆብ ልጆች ልደት |
| 30፥25-31፥1 | የያዕቆብ ላባን መብለጥ |
| 31፥2-32፥2 | የያዕቆብ ላባን ትቶ መሄድ |
| 32፥3-33፥20 | የያዕቆብና የኤሳው እርቅ |
| 34፥1-31 | የዲና መደፈርና የወንድሞቹዋ በቀል |
| 35፥1-29 | የያዕቆብ መመለስና የይስሐቅ ጉዞ ፍጻሜ |

36፥1-371 የኤሳው ትውልድ

37፥2-50፥26 የያእቆብ ትውልድ

| | |
|---|---|
| 37፥2-36 | የዮሴፍ በወንድሞቹ ወደ ግብፅ መሸጥ |
| 38፥1-30 | የይሁዳ በትእማር መማረክ |
| 39፥1-47፥31 | ዮሴፍ በግብፅ |
| 48፥1-50፥26 | የያዕቆብና የዮሴፍ የመጨረሻ ቀናቶች |

1.8. የመጽሐፉ መሠረታዊ ትምህርት

1. የእግዚአብሔር የሁሉ አስገኝነትና መጋቢነት።
2. የኃጢአት ወደ አለም መግባትና የሰው ልጅ ውድቀት
3. የኃጢአት ውጤትና የእግዚአብሔር የምህረት ምልክት
4. እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን